# ግልፅና ወቅታዊ አደጋ

የሶማሊያን ጉዳይ አስመልክቶ ለተነሳው ጥያቄ የተለያዩ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስቀመጥ ይቻላል፤ አንደኛ በሶማሌዎች መካከል ያለው አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ የማድረግ ጉዳይና በኢትዮጵያ ላይ የተደቀነው፣ የተቃጣው ጥቃትና አደጋን በተመለከተ ሁለቱም ጉዳዮች በከፊል የተሳሰሩ ቢሆኑም የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው ጉዳዮች ናቸው።

በከፊል የተሳሰሩ ናቸው የምንልበት ምክንያት ከሽግግር መንግሥቱ ጋር ግጭት የተቀሰቀሰው ራሱን የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት ብሎ የሚጠራው ስብስብ የግጭትና የጦርነት ፖሊሲውን ትቶ ከሽግግር መንግሥቱ ጋር በሰላም ተደራድሮ ችግሩን መፍታት ከቻለ ይህ ኃይል በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሰውን ጥቃትና አደጋ ሊቀንስ ወይም ሊቀይር ይችላል የሚል ተስፋ አለ፤ በዚህ ምክንያት ሁለቱ ጉዳዮች የተሳሰሩ ናቸው።

በሌላ በኩል ሲታይ ግን ሁለቱም የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። በሶማሌዎች መካከል ያለውን ቅራኔ የመፍታት ጉዳይ የሶማሌ ሕዝብን ይመለከታል። ሌሎች ሀገሮች የሶማሌ ሕዝብን መደገፍ የሚችሉ ቢሆንም የሶማሌ ሕዝብን ተክተው ችግሩን ሊፈቱ አይችሉም። ከሶማሊያ በመነሳት በሀገራችን ላይ የሚቃጣው ጥቃት የኢትዮጵያ ሕዝብንና መንግሥትንም ይመለከታል። ሁለቱ በከፊል የተሳሰሩ ጉዳዮች ቢሆኑም በባህሪያቸው የተለያዩ እንደሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። የሶማሊያ ጉዳይን በምናይበት ወቅት አንዱ መሠረታዊ ሐቅ ይህ ነው። ሁለተኛ የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረትን እየመራው ያለው ኅብረቱ በአጠቃላይ ሳይሆን የጅሃዲስቶች ቡድን ነው። ቡድኑ በኢትዮጵያ ላይ በአሁኑ ሰዓት ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ደቅኗል። (ክሊር ኤንድ ፕሬዘንት ዴንጀር) ይህን የምንልበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ።

1ኛ/ ይህ ቡድን በኢትዮጵያ ላይ የጅሃድ ጦርነት አውጇል። ጦርነቱን ያወጀው በድብቅ አይደለም- በይፋ ነው፤ ጦርነቱን ያወጀው አንድ ጊዜ አይደለም በተደጋጋሚ ነው። የጅሃድ ጦርነቱን በይፋ እና በተደጋጋሚ በማወጁ በኢትዮጵያ ላይ ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ደቅኗል።

2ኛ/ ይህ ቡድን በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ሶማሊኛ ተናጋሪ ሕዝቦች በሙሉ በጅሃዲስቶቹ መንግሥት ሥር እንዲተዳደሩ አደርጋለሁ ብሎ አውጇል።ይህ አዋጅ ኢትዮ ጵያን ብቻ የሚመለከት አይደለም፤ ኬንያንም ይመለከታል፣ ጅቡቲንም ይመለከታል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያንም ይመለከታል። የኢትዮጵያ ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው ሆኖ ሳለ አንድ በጐረቤት አገር ያለ ቡድን በጉልበት፣ በኃይል የኢትዮጵያን ሰፊ ክልል በግዛቱ ውስጥ አስገባለሁ ብሎ ማወጁ የዓለም አቀፍ ሕግን ከመፃረሩ ባሻገር በኢትዮጵያ ሰላምና ሉዓላዊነት ላይ የተቃጣ ወቅታዊ እና ግልፅ አደጋ ነው። ይህ አዋጅ በድብቅ እየተሠራ ያለ አይደለም፤ በይፋ የታወጀ አዋጅ ነው። አንድ ጊዜ ብቻ የተባለ አይደለም፤ በተደጋጋሚ ጊዜ የተባለ ነው።

3ኛ/ ይህ ቡድን የታጠቁ ፀረ ሰላም የኢትዮጵያ ኃይሎችን በአካባቢው መጠለያ በመስጠት፣ በማሠልጠን፣ በማስታጠቅ እና ወደ ሀገራችን በማስረግ በሀገራችን ላይ

ቀጥተኛ ጥፋት እየፈፀመ ያለ ኃይል ነው። ይህ ተግባር፣ ይህ ወንጀል ተፈጽሟል የምንለው እኛ ብቻ ሳንሆን የተባበሩት መንግሥታት የላከው የአካባቢውን ጉዳይ፣ የአካባቢውን ሰላም የሚቆጣጠረው አካል በቅርቡ ባቀረበው ሪፖርት በግልፅ ያመለከተው ጉዳይ ነው።

4ኛ/ ይህ የጅሃዲስቶች ቡድን በኢትዮጵያ ላይ የጥቃት አደጋ እያደረሰ ያለው፣ ጥቃት እየፈፀመ ያለው በራሱ አቅም ብቻ በመተማመን ሳይሆን ከኤርትራ መንግሥትና ከሌሎች ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በመተባበር እንደሆነ ይታወ ቃል። በምስጢር የተፈጸመ ጉዳይ አይደለም፤ የአደባባይ ምስጢር ነው። ሁሉም የሚያውቀው ነው፣ የተባበሩት መንግ ሥታትም በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት በግልፅ ያመለከተው ነው። ይህ ኃይል ከሌሎች ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ጥቃቱን መፀፈሙ በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለው አደጋ መጠኑ እንዲጨምርና የከፋ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል።

እነዚህን አራት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ይህ ኃይል በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ላይ ግልፅና ወቅታዊ አደጋ (ክሊር ኤንድ ፕሬዘንት ዴንጀር) የሚያስከትል ኃይል ሆኖ ይገኛል። ይህንን ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ለመቋቋም መንግሥት እየተከተለ ያለው ፖሊሲ በመጀመሪያ ደረጃና በዋናነት ከዚህ ኃይል ጋር በመ ወያየት፤ ከዚህ ኃይል ጋር በመደራደር በላያችን ላይ እየቃጣ ያለውን ጥቃት እንዲያስወግድ መምከር፣ መወያየት መደራደር ነው። ማንኛውም ችግር በመጀ መሪያ ደረጃ መፈታት ያለበት በውይይትና በድርድር ስለሆነ፤ ከማንም ወገን ጋር ከጅሃዲስቶች ጋርም ቢሆን መጀመሪያ መወያየት እና መደራደር ያስፈልጋል። የሰላም አማራጭ ሲዘጋ ብቻ ነው ሌላ አማራጭ ሊታሰብ የሚቻለው።

ስለሆነም ከእነዚህ ጅሃዲስቶች ጋር፣ በሀገራችን ላይ የጅሃድ ጦርነት ካወጁት ጅሃዲስቶች ጋር በተለያዩ ወቅቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካዮች ተገናኝተው አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ከመሰንዘር እንዲቆጠቡ ለማግባባትና ለማስረዳት ሙከራ ተደርጓል፣ ከአንዴም ሁለቴ። እስካሁን ድረስ ሙከራው አልተሳካም። ይሁንና ባለፈው ጊዜ በሌላ ምክንያት እንደገለፅኩት 11ኛው ሰዓት ያለፈ ቢመስልም እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ተገናኝተን በኢትዮጵያ ላይ እየፈፀሙ ያሉትን ጥቃት እንዲያቆሙ ለማድረግ በሰላማዊ መንገድ ይህንን ለማድረግ ከመሞከር ወደኋላ አንልም። ይህ የመጀመሪያውና በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ተመራጭነት ያለው መፍትሔ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ በሰላማዊ መንገድ ችግሩን ለመፍታት በኢትዮጵያ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ጥቃት ለማስቆም የያዝነው ጥረት ባይሳካ ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ጉዳይ ማየት ይኖርብናል። እንደሚታወቀው ሁሉ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ማንኛውም ሀገር በላዩ ላይ እንደዚህ ዓይነት አደጋ ሲደቀን፣ ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ሲያጋጥመው ማንም የማይሰጠው ማንም የማይከለክለው የማንም ፍቃድ የማያስፈልገው ራሱን የመከላከል መብት አለው፤ ማንኛውም አገር አደጋውን ለመቋቋም ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ የመውሰድ መብት አለው። ትርፍ ኃይል መጠቀም አይችልም፤ ተመጣጣኝ የሆነ እርምጃ የመውሰድ መብት ግን ማንም ሊሰጠው የማይችል መብት አለው እያንዳንዱ ሀገር። ይህንን መብታችንን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችል በቂ ዝግጅት ማድረግ ሁለተኛው የመፍትሔ አማራጭ ነው። ይህንንም በተመለከተ መንግሥት ተፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ ነው፤ አድርጓልም። አሁንም ቢሆን

የመንግሥት ምርጫ ጅሃዲስቶቹ በሀገራችን ላይ እየፈፀሙ ያሉትን ጥቃት በአፋጣኝ እንዲያ ቆሙ ማድረግ፣ ይህንን በውይይት ማስፈፀም ነው። የሰላሙ አማራጭ 11ኛው ሰዓት ቢያልፍም ተሟጥጧል ብለን አናም ንም። እስኪሟጠጥ ድረስ የሰላሙን አማራጭ በቅድሚያ ይዘን መግፋት አለብን ብለን እናምናለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥቃት እየተፈፀመ ባለበት ወቅት ዓይናችንን ጨፍነን ምናልባት በምክር ወይም በውይይት ይወገ ድልን ይሆናል ብለን እጅና እግራችንን አጣጥፈን ልንቀመጥ አንችልም፤ ስለሆነም ዝግጅት አድርገናል። በሚቀጥለው ወቅት መንግሥት የሚከተለው ፖሊሲ በአንድ በኩል የሰላሙን አማራጭ የማሟጠጥ በሌላ በኩል ደግሞ የሰላሙ አማራጭ ዝግ ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያን ሰላምና መረጋጋት ለመጠበቅ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት በላያችን ላይ የተደቀነውን ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ለመመከት የሚያስችል ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ ይሆናል።

ይህ በኢትዮጵያና በጅሃዲስቶቹ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን፤ በጅሃዲስቶቹÂ በሽግግር መንግሥቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የኢትዮጵያ አቋም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከወሰደው አቋም በምኑም የሚለይ አይደለም።

1ኛ. በአፍሪካ ኅብረትና በተባበሩት መንግሥታት ዕውቅና ያገኘውን የሽግግር መንግሥት እንደግፋለን።

2ኛ. የሽግግር መንግሥቱ ከእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ጋር ያለውን ልዩነት በውይ ይት በድርድር እንዲፈታ እንደግፋለን።

3¾. ይህ ድርድር የሽግግር ቻርተሩን፣ የሽግግር መንግሥት ተቋሞችን መሠረት ባደረገ አኳኋን በሰጥቶ መቀበል መርህ መከናወን ይገባዋል ብለን እናምናለን።

ሶማሊያን በተመለከተ በመንግሥት በኩል እስካሁን የተሠሩ ሥራዎችና ያለው አቋም ይህን ይመስላል። በዚሁ አጋጣሚ ምክር ቤቱ ለጅሃዲስቶቹም ሆነ ለሌላው የሚመለከተው አካል የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያን ሕዝብ የወከለው ምክር ቤት ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ ያሉት ዕድሎች በሙሉ እንዲሟጠጡ ፍላጐቱ መሆኑ፣ ከዚህ አልፎ ጥቃቱ የሚቀጥል ከሆነ ግን መንግሥት አስፈላጊውንና ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ምክር ቤቱ የሚደግፍ መሆኑን በይፋ ቢያስታውቅ ይጠቅማል የሚል እምነት አለኝ፤ ስለሆነም ምክር ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም በይፋ እንዲያሳውቅ ጥያቄዬን አቀርባለሁ።

ሠይፈ ደርቤ

አዲስ ዘመን, ህዳር 16/1999 ዓ.ም